# የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት

## ሮማዊ መሠረቶች*

በፒተር ኤች ሳንድ**

በኢትዮጵያ ሕግና በአውሮፓ ሕግ ፥ በተለይ በሮማውያን ሕግ ፤ መሐከል ያለው ዝምድና ብዙ ጊዜ የተነሳ ሲሆን ፥ በይበልጥ የኢትዮጵያን የ፲፱፻፷ የፍትሐ ብሔር ሕግ ባረቀቁት በፕሮፌሰር ረኔ ዳቪድ የኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት ሮማዊ ምንጭ ተለይቶ ተጠቅሶ አል ።[1***] በሮማዊው ንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት የተደረጉ ሙከራዎች ቢኖሩም ቅሉ እስከምናውቀው ድረስ ከሆነ ግን በሮምና በኢትዮጵያ ነገሥታት መሐከል የነበረው ቀጥተኛ ግንኙነት በጣም የተቀራረበ ሆኖ አያውቅም[2] ። ይህ የተባለው ዝምድና መኖሩ ሳይረጋገጥ ይሆን ድብስብስ የሆነ ዝምድና መነሻ በማድረግ ፥ ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሕግ ማርቀቅ አስገራሚ ይሆናል ። ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ጥንታዊ ሕግና በሮማ ጥንታዊ ሕግ መሐከል ያለውን እውነተኛ መተሳሰር ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራ ነው ፣

## ፩ ጽሑፎች ፤

የሕግ ታሪክ በማነጻጸር በሚደረግ ዓለም አቀፍ ጥናት ኢትዮጵያ አሁንም ቢሆን የታወቀች አገር አይደለችም ።[3] ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የቋንቋ ገደብ ሲሆን ለሕግ ንጽጽር ጥናት በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን መረዳት አይቻልም ነበር ። የዓለም አቀፍ ምሁራን የግዕዝ ቋንቋ ዕውቀት ስለአልነበራቸው የሕግ ንጽጽር ጥናት ለማድረግ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን መመርመር አልቻሉም ። በእንጻሩም ሊቃውንቱ የላቲን ቋንቋ ያውቁ ስለነበር ሮማዊ መጻሕትን ለመመርመር ተመሳሳይ ችግር አልገጠማቸውም ።

### ግምቶች

ስለዚህ ሽርማንና ዌግኖር ከሃምሳ ዓመት በፊት የአሁኑ የሐበሻ ሕግ በጀስቲንያን ሮማዊ ሕግ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ጥንታዊ ፍጹም ሮማዊነቱን[4] አጥቶም ከሮማንይስክ ዓይነት (Romanseque type)[5] ውስጥ የሚውል ስለመሆኑ ስላተቱት ጉዳይ ማስረጃ ሊያቀርቡ አይችሉም ። ምናልባትም የዚህ ግምታቸው መሠረት የሆነው አንዳንድ የውጭ መንገደኞች በ፲፮ ነኛው ምዕተ ዓመት ለአንድ የአልታወቀ ፍትሐ ነገሥት የሚል የግዕዝ መጽሐፍ "የጀስቲንያን ኮድ ኢትዮጵያዊ ትርጉም"[6] የሚል መግለጫ የሰጡት ይሆናል ። የእንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናዊ የሆነው ጐባት ይህ እምነት ሐበሾች የመጽሐፉን ደራሲነት "ከጀስቴንያን ይልቅ ለቆስጠንጢኖስ"[7] ይሰጡታል ካለው ሳይመነጭ አይቀርም ። ከዚህ በኋላ የተነሱት ጸሐፊዎች ፍትሐ ነገሥት የሙሴን መጻሕፍትና የወንጌልን ትዕዛዛት ከጀስቴንያን ሕግ ጥቂት ክፍሎች ከሞላ ጎደል በማሟላት[8] "ወይም" የሙሴን የጥንት ጽሑፍ ፥ ደራሲዎቻቸው ካልታወቁ መጻሕፍት (apocrypus) እና ከሐዋርያቶች ጉባኤ (ሲኖዶስ) እንዲሁም ከቲዎዶሲያስና ከጀስቲንያን ሕግጋት[9] አጠናቅረዋል የሚል አስተያየት ጨምረዋል ።

### ያልታተሙ ጽሑፎች

ኢዝንበርግ በ፲፰፻፵፪[10] የፍትሐ ነገሥትን ቅጅ ወደ ለንደን ከላከ በኋላ ብሩስ በ፲፯፻፸፬ ከወሰዳቸው ጽሑፎች መሐከል የተሳሳተ መግለጫ የሰጠበትና ቀደም ሲል የተዘጋጀ ያልታተመ ጽሑፍ እንደ ነበረ ደልማን አግኝቷል[11] ። ሮሸር ደ ኸርኩርት ደግሞ ከሸዋ ንጉሥ ለፈረንሳይ ንጉሥ በገጸ በረከትነት የተላከውን የዚህን "የተከበረ መጽሐፍ" ቅጅ ፓሪስ አምጥቷል ።[12] ሩፔልም በአንድ ያልታተመ ጽሑፍና ከኢትዮጵያዊው ምሁር ከሊቅ አትክሚ[13] በግል ባገኘው መረጃ በመመርኮዝ የጽሑፉን ማውጫ አጭር መግለጫ በ፲፰፻፴ አሳትሟል ። በሩቅ ምሥራቅ ትምህርት የታወቀው ቮን ኤዋልድ ደግሞ በሚስዮናዊው ክራፍ አማካይነት አንድ ሌላ ያልታተመ ጽሑፍ አግኝቶ በ፲፰፻፵፩ መዝግቧል ።[14]

በሉርድ ናፒር የ፲፰፻፷፰ ወታደራዊ ዘመቻ የእንግሊዝ ሠራዊት አጼ ቴዎድሮስን ድል መትቶ የመቅደላን ቤተ መንግሥት ግምጃ ቤት ከዘረፈ በኋላ በርከት ያሉ ያልታተሙ ጽሑፎች ተገኝተዋል ። የእንግሊዝ ሙዚየም (ቤተ መዘክር) ባልደረባ ሪቻርድ ሆልምስ በከፍተኛ ተጫራችነት በተከፈለበት የተዘረፈው ጽሑፍ በቦታው በጨረታ ተሸጧል ።[15] ራይት የተባለው በ፲፰፻፸፯ ባወጣው የመጻሕፍት ዝርዝር በሙዚየሙ ውስጥ የነበሩ ከአሥራ አንድ ያላነሱ የፍትሐ ነገሥት ያልታተሙ ግልባጮች መዝግቧል ።[16] በአውሮፓ ቤተ መጽሐፍት የተረጋገጡ ሃያ የፍትሐ ነገሥቱ ያልታተሙ

---

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት ቀኖች በሙሉ እ ኤ አ ዓ/ም ናቸው ። ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ለመለወጥ ሰባት ወይም ስምንት ዓመት በመቀነስ ሊሰላ ይችላል ።

** ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር የነበሩ ሲሆን አሁን በዓለም የምግብ ድርጅት ይሠራሉ ።

*** የጽሑፉ ግርጌ ማስታወሻ በዚህ ትርጉም ያልተገለበጠ ስለሆነ የዚህን ጽሑፍ የእንግሊዝኛ ቅጂ በመመልከት ማገናዘብ ይቻላል ።

ጽሑፎች እንደሚገኙ ኮንቲ ሮሲኒ መዝግቧል ።[17] በ፲፱፻፲ ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ ሃያ አራት ይገኙ ነበር ።[18] ዛሬ በአውሮፓ ቤተ መጻሕፍት የሚገኙት ቁጥር ወደ ፴ የሚጠጋ ሲሆን (በእርግጥ ግራፎን ከሚለው ከአምስት በላይ[19]) በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የሚገኙ ያልተመዘገቡ የእጅ ጽሑፎች ቁጥር ከመቶ በላይ እንደሚሆን በሚያስተማምን ሁኔታ ሊገመት ይችላል ።[20]

## የታተሙ ጽሑፎች

ተከታዩም አቢይ የጽሑፍ ምርምር ቢሆን በአጋጣሚ በወታደራዊ እንቅስቃሴ ምክንያት የተጀመረ ነው ። በ፲፰፻፹፰ ኢትዮጵያን ለመያዝ ለነበረው መሰናዶ አካል በማድረግና ለቅኝ ግዛታዊ የዳኝነት ሥራ አካሄድ መገልገያ እንዲሆን ፍትሐ ነገሥትን አስተካክሎ እንዲተረጉም የኢጣሊያ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር በሩቅ ምሥራቅ ትምህርት የታወቀውን ኢኛዚዮ ጉዊደን ሰየመ ። የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት በ፲፰፻፹፰ በአጼ ምኒሊክ ድል ከተመታ በኋላ በግዕዝ ቋንቋ የተዘጋጀው የፍትሐ ነገሥት ግልባጭ ቀደም ሲል እንደታቀደው ጊዜውን ከሞላ ጎደል ሳያዛንፍ በ፲፰፻፺፫ ታትሞ ወጣ እንዲሁም የኢጣሊያንኛው ትርጉም በ፲፰፻፺፱ ተከታትሎ ታተመ ።[21] ይህም ቀደም ሲል በአንድ ፈረንሳይ ቤተ መጽሐፍት የመጽሐፍ ዝርዝር[22] በቁንጽል ከታተመው በስተቀር በወቅቱ ከነበሩት የእጅ ጽሑፎች መሐከል ምርጥ የሆኑትን ለሰባት ዓመታት እጅግ አድካሚ በሆነ መንገድ በማነጻጸር በኢትዮጵያዊው ምሁር በክፍለ ጊዮርጊስ እርዳታ ጭምር የተዘጋጀ የመጀመሪያው የታተመ ግልባጭ ነው ። ይህ እትም እስካሁን ከተዘጋጁት ትክክለኛ ነው ተብሎ የታመነበት ሲሆን ፤ ትክክለኛ ነው ተብሎ የታመነበት በመሆኑም ፤ በ፲፱፻፴ የወጣው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፍትሐ ነገሥቱን ሲጠቅስ የጉዊዱን ጽሑፍ ገጽ በገጽ በማመልከት ተጠቅሞበታል ።[23] "አፊሲያላዊ" የአማርኛ ግልባጭ መታተም በ፲፱፻፳፰ አዲስ አበባ ተጀምሮ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መሐከል በነበረው ጦርነት ከተቋረጠ በኋላ በመጨረሻ በ፲፱፻፴፬ ተጠናቋል ።[24]

## ትርጉም

የፍትሐ ነገሥቱ ቁንጽል የላቲን ትርጉሞች በአርኖልድ (፲፰፻፵፩) እና በችማን (፲፰፻፶፱) ታትመዋል ።[25] የኢጣልያንኛ እትም ቀደም ሲል በደስቲፋኖ በ፲፰፻፺፯-፺፱[26] የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ቀደም ሲል የተዘጋጀው ትርጉም ሬይን (፲፱፻፲) በአጭሩ ላዘጋጀው የጀርመንኛ ትርጉሙ መሠረት ሆኖታል ።[27] ሆኖም ከሁሉም የጉዊዲ ትርጉም በይበልጥ የሚያስተማምን ነው ። ይህትርጉም ደ ካስትሮ (፲፱፻፲፪) ፤ ማውሮ ዳ ሊዎኔሳ (፲፱፻፴፩) እና ሮስካነቮሬ (፲፱፻፴፬)[28] በተከታታይ ባዘጋጁዋቸው የኢጣሊያንኛ ትርጉሞች በይበልጥ የተጠቀሙበት ሲሆን በጳውሎስ ዘ ጻድዋ ተተርጉሞ በስትራውስ በ፲፱፻፷፰[29] ለተዘጋጀው የመጨረሻ የእንግሊዝኛ እትም ዋና መሠረት ሆኗል ።

## ይዘት

በከፊል ለንጽጽር ከሚያገለግሉት (አንቀጽ ፲፰ ምዕራፍ ፪ ጉልት) (Charitable Legacies)[30] በስተቀር የፍትሐ ነገሥቱ የመጀመሪያ ክፍል (አንቀጽ ፩-፳፪) መንፈሳዊ ሕግን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ብቻ ይይዛል ። ሁለተኛው ክፍል (ፍትሐ ሥጋዊ-አንቀጽ ፳፫-፶፩) እና አባሪው ግን ስለሚከተሉት ያወሳሉ ።[31] ፳፫ ፤ ምግብ ፣ ልብስ ፣ የመኖሪያ ሥፍራና ለክርስቲያኖች ተገቢ ስለሆነው መተዳደሪያ (ሥራ) ። ፳፬ ፤ መተጫጨት ፣ ጥሎሽ ፣ ጋብቻና የጋብቻ መፍረስ ፳፭ ፤ ዕቁባት ማኖር እንደማይገባ ። ፳፮ ፤ ስጦታ ። ፳፯ ፤ ብድር ፣ መያዣና ዋስትና ። ፳፰ ፤ ለጥቅም (ለአገልግሎት) ስለሚሰጥ ብድር ። ፳፱ ፤ አደራ ። ፴ ፤ ምግብና ፴፩ ፤ ባርነትና ባርያን ነፃ ማውጣት ። ፴፪ ፤ ሞግዚትነት ፴፫ ፤ መሸጥ ፣ መግዛትና ተመሳሳይ ጉዳዮች ። ፴፬ ፤ ሽርክና (ተሳትፎ) ፴፭ ፤ በኃይል ማስገደድ ። ፴፮ ፤ ኪራይ ። ፴፯ ፤ ሕንፃ ፣ መንገድና ውኃ ። ፴፰ ፤ የንግድ ሥራዎች ። ፴፱ ፤ ብድርን (ዕዳን) ማመን ። ፵ ፤ የጠፉና ባለቤት የሌላቸው ዕቃዎች (ቁሳቁስ) ፵፩ ፤ ኑዛዜ ። ፵፪ ፤ ውርስ ። ፵፫ ፤ ዳኝነትና የዳኝነት ሥርዓት ። ፵፬ ፤ የንጉሥ መብትና ግዴታ ።፵፭ ፤ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳን የተለያዩ ድንጋጌዎች ። ፵፮ ፤ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የማንሳት ፣ የክህደትና የአስማት ወንጀል ቅጣት ድንጋጌዎች ። ፵፯ ፤ የዝሙት ወንጀል የቅጣት ድንጋጌዎች ። ፵፰ ፤ የሌብነት ወንጀል የቅጣት ድንጋጌዎች ። ፵፱ ፤ የስካር ፣ አራጣ እና የተለያዩ ወንጀሎች የቅጣት ድንጋጌዎች ። ፶ ፤ ውርስ ፤ ግዝረት ፤ ኑዛዜና የካህናት ሕግ የማውጣት ሥልጣን የቤተ ክርስቲያን ደንቦች ። አባሪ ስለውርስ ።

## ፪ ፤ ምንጮች ።

ፍትሐ ነገሥት በአገር ውስጥ መሠረት የሌለው መሆኑ በአማርኛ አፈ ታሪክ የባህር ሕግ ማለትም "ከባሕር ማዶ የመጣ ሕግ" ተብሎ በመጠራቱ ይታወቃል።[32] በአንድ በሕዝብ ዘንድ በታወቀ አፈ ታሪክ የሕግ መጽሐፍ (በሮማ ንጉሠ ነገሥት) ቆስጠንጢኖስ[33] ዘመነ መንግሥት ከሰማይ እንደወረደ ሲነገር ሌሎች ደግሞ ሠለስቱ ምዕት እንዳወጡት ይናገራሉ ። የፍትሐ ነገሥቱ የግዕዝ መቅድም በኒቂያ ጉባኤ (፫፻፳፭ ዓ/ም) ተሰብስበው የነበሩት ፫፻፲፰ የኦርቶዶክስ ጳጳሳት በንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ጥያቄ የሕግ መጽሐፉን እንዳዘጋጁ በግልጽ የሚናገር ሲሆን የሁለቱም አፈ ታሪኮች ምንጭ የዚሁ የስሚ ስሚ ቅጅ ነው ።[34] በ፲፱፻፷፯ የአማርኛ እትም እንደተገለጸው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ታሪክ ኢትዮጵያዊው ንጉሠ ነገሥት ዘርዓ ያዕቆብ (፲፬፻፴፬-፲፬፻፷፰) መጽሐፉን ከግብጽ አስመጥቶ ወደ ግዕዝ[35] ቋንቋ እንዳስተረጐመው ይነገራል ።[36] ፍትሐ ነገሥቱን ወደ ግዕዝ የተረጐመው ሰው ግብፃዊው ክርስቲያን ኢብን አል አሳል ባጠናቀረው የአረብኛው ጽሑፍ መጠቀሙ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባህል ተጠቅሶአል ።[36]

## የኮፕት የሕግ መጻሐፍ (Coptic Nmocanon)

እንግዲህ ያለቦታቸው የተጠቀሱት አንዳንድ ግልጽ ስህተቶች ከተወገዱ የፍትሐ ነገሥት የቅርብ ምንጭ በቂ በሆነ የታሪክ ማረጋገጫ ሊታወቅ ይችላል ። ከመቅድሙ የመጀመሪያ ክፍልና ከአባሪው[37] በስተቀር መጽሐፉ በመጀመሪያ በአረብኛ ከተጻፈውና ከዝነኛው የኮፕት "የሕግ መጽሐፍ" ቃል በቃል የተተረጎመ ነው ።[38] የዚህም መጽሐፍ ሠላሳ የሚሆኑ የታመኑ ያልታተሙ ጽሑፎች በአውሮፓና በግብጽ ቤተ መጻሕፍት ሲገኙ ሁለት እትሞች በ፲፱፻፰ እና በ፲፱፻፳፪ ወጥተዋል ።[39] የዚህ የሕግ መጽሐፍ ደራሲ የፍትሐ ነገሥቱ መግቢያ እንደሚያመለክተው በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት አልነበረም ። የኮፕት ሥነ ጽሑፍ በገነነበት በ፲፫ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ክፍል ይኖር የነበረ ፣ የኮፕት ክርስቲያን ሊቅ የሆነ አስ-ሳፍ-ኢብን-አል-አሳል ነው ። እርሱም ለሰባ አምስተኛው የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ቄርሎስ ሳልሳዊ ኢብን ላቅላቅ (፲፪፻፴፭-፲፪፻፵፫) የሕግ አማካሪ ሆኖ ከማገልገሉም በላይ በርከት ያሉ በተለይም ሃይማኖትን የሚመለከቱ ጽሑፎች አዘጋጅቷል ።[40] "አሳላዳውይን" (Assalades) በመንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችና በትምህርት (ምሁርነት) ከፍተኛ ደረጃ የነበራቸው ጥንታዊ የኮፕት ቤተሰብ (አውላድ አል አሳል) ነበሩ ።[41] ኢብን አል-አሳል በሚል ስም የሚታወቁ ቢያንስ አራት ወንድማማቾች ሲኖሩ ከነዚህ መሐከል ሦስቱ በሥነ ጽሑፍ የታወቁ ስለነበሩ የትኛው ኢብን አል አሳል የሕግ መጽሐፉን እንደጻፈ መጠነኛ ውዥንብር ነበር ። በቅድሚያ በተዘጋጀውና እምብዛም ባልታወቀው ቅጅ ደራሲነት የሚታወቀው ታናሽየው አል ሙታማን (አድ-ደውላ) አቡ ኢሳቅ ኢብራሂም ኢብን አል-አሳል[42] ሲሆን ሁለተኛው አል አሳድ አቡል-ፋለግ ሂሊህ ኢብን አል አሳል የውርስ ሕግ ማብራሪያ እንደደረሰ ይታወቃል ።[43] የሚታመነው ቅጅ ደራሲ ግን ታላቅየው አስ ሳፍ ኢብን አል-አሳል እንደሆን በሚገባ የተረጋገጠ ይመስላል ።[44] ጥንታዊ ከሆኑት የእጅ ጽሑፎች በአንዱ እንደተመለከተው የመጽሐፉ ዝግጅት በመስከረም ፲፪፻፴፱ ተጠናቅቋል ። ሕግን እንደገና በማብራራት ረገድ ለትምህርታዊ ተጠቃሽነት የታቀደ ቢሆንም መጽሐፉ ወዲያውኑ በዳኝነት ሥራ አካሄድ በግንባር ቀደም በመጠቀስ የሚያገለግልና የግብፅ ኮፕት ቤተክርስቲያን የመተዳደሪያ ጽሑፍ [45](textus receptus) ሆኗል ።

የኮፕት ቋንቋ በሕግ ሥነ ጽሑፍ የነበረው መገልገያነት በ፲፩ኛው ምዕተ ዓመት ቀርቶ ስለነበር የዘመኑ የጥንት የሕግ ጽሑፎች የተዘጋጁት በአረብኛ ነው ። እነዚህም ጥንታዊ የሕግ ጽሑፎች በግሪክ-ሮማን ዘመን[46] እንደሚገኘው ጥንታዊ የኮፕት ፓፓይር (Papyri)[47] ሳይሆን በአጠቃላይ "የክርስቲያን አረብኛ ሥነ ጽሁፍ" ተብሎ ከሚጠቀሰው ክፍል ናቸው ። በግብፅ ውስጥ በእስላም አስተዳደር ሥር እንደነበሩት እንደ ሌሎቹ የክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ሁሉ ኮፕቶችም በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ራሳቸውን የማስተዳደር በተለይም የቤተ ሰብ ሕግንና ውርስን[48] በሚመለከቱ ጉዳዮች የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች የፍርድ ሥልጣን (episcopales audientia) ነበራቸው ። ይህም በኢትዮጵያ[50] የእስልምና ፍርድ ቤቶች ካላቸው ከፊል ነፃነት (አውቶኖሚ) የሚመሳሰል ነው ። ሆኖም አጠቃላይ ከሆነው የእስልምና የሸሪያ ሕግ ጋር ሲነጻጸር ለምዕመናኑ ዝርዝር ያለ ሥርዓተ ሕግ አላወጣም ። የግብጽ መለካውያን (Melechites) በቅዱሳት መጻሕፍትና በተለያዩ መንፈሳዊ ምንጮች ሊያገኙ ከሚችሏቸው ተራ የግብረ ገብነት ደንቦች ባሻገር በ፩ ሺህ ፩፻ አካባቢ "ለሰዎች ሕግ" (Personal Law) ባደረጉት ፍለጋ የግሪክ ባዛንታይን የፍትሐብሔር ሕጎችን እየመረመሩ ወደ አረብኛ መተርጎም ጀመሩ ።

ሆኖም የኮፕት ማኅበረሰብ አብዛኛዎቹን ትርጓሜዎችና ቅንጅቶች[50] የተጠቀመውና የተቀበለው በሃይማኖት ትምህርቱ ረገድ አንዳንድ ማስተካከያ በማድረግ ነው ። በዚህ ዓይነት በኮፕት ቤተ ክርስቲያን እንደ ከሃዲ የሚቆጠሩ የባዛንታይን ነገሥታት ከርዕሱ ተሰርዘው ሕጎቻቸውም ለታላቁ ቆስጠንጢኖስና ለኒቂያው ጉባኤ ተሰጥተዋል ፡ ይህ በዕምነት ላይ የተመረኮዘ የማመሳሰል ድርጊት ሬዶል[51] እንደገመተው ባለማወቅ የተፈጸመ ሳይሆን ሆን ብሎ የተደረገ ነው ። ይህም በዘመኑ የነበረውን የኮፕት ትምህርት ሃይማኖት ቃል በቃል ለሚጠቅሰው[52] በፍትሐ ነገሥቱ መቅድም መጀመሪያ ክፍል ላለው ቦታውን የሳተ ሐሳብና መጽሐፍም ለተሰጠው "የነገሥታት ሕግ" የሚል ቁንጽል ስያሜ ምክንያት ሆኖአል ።

## የባዛንታይን የሕግ መጻሕፍት

ኢብን አል-አሳል የሕግ መጻሕፉ ተመሠረተባቸው የሚላቸውን ምንጮች በመግቢያው አመልክቷል ። ለመጀመሪያው መንፈሳዊ ክፍል ከቅዱሳት መጻሕፍትና የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ደንቦች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑት መሠረት ሲደረጉ[53] የሁለተኛው (ሥጋዊ) ክፍል ዋና ምንጭ ደግሞ "በንጉሡ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ ቤተ መንግሥት"[54] ተጽፎአል የሚባለው አራት መጻሕፍት ያሉት "የነገሥታት ሕግ" ነው ።

ከነዚህ አራት መጻሕፍት ለሕግ ንጽጽር ተፈላጊነት ያላቸው ሦስቱ ብቻ ሲሆን አራተኛው "የብሉይ ኪዳን ትእዛዛት"[55] የሚባለው ነው ። "የነገሥታት ደንብ" አንደኛ ፤ ሁለተኛና ሦስተኛ መጻሕፍት ፤ በሕግ መጽሐፍና በኢትዮጵያ ውስጥ በተተረጎመው በምኅጻረ ቃል ጠስ (TS) ፤ መክ (MAK) እና መጅ (MAG) ተብለው የተጠቀሱት ፣ የፍትሐ ነገሥቱ ትክክለኛ ሥጋዊ ምንጮች ናቸው ። የእነዚህን ሦስት መጻሕፍት አመጣጥ ለማወቅና ለመለየት ሲባል በሕግ ታሪክና ቋንቋ ሊቃውንት ብዙ ምርምርና ክርክር ተካሂዶአል ። ሬንዶ በ፲፱፻፲፫[56] ሲጽፍ በመጀመሪያ በነርሱና በባዛንታይን ሮማ ሕግ መሐከል ግንኙነት እንዳለ አመልክቷል ። እነዚህ ደንቦች (ሕጎች) ከግሪክ የሕግ መጻሕፍት ፤ ከቴዎዲዮስና ጀስቲንያን ጥንታዊ ጽሑፎች (Codex) ፤ አዳዲስ ሕጎች (Digesta) እና ሕገ መንግሥቶች (Novella) እና ባሲሊካ (Basilica) በሚባል መጠርያ ከታወቁ ሕግጋት የተውጣጡ እንጂ ሌሎች አዲስ ሕጎች ያልነበሩ ሲሆን ሕጎቹ ከላይ በተ

ጠቀሰው አኳኋን ተቀናጅተው በክርስቲያኖች መሐከል የሚነሱ ክርክሮችን ለመዳኘት ያገለግሉ ነበር ሆኖም ሥርዓት ባለው መንገድ በተከታታይነት የተካሄዱ ጥናቶች ከዚህ የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝተዋል ።

## ሀ/ ፕሮሼሪየን (Procheiron)

"የነገሥታቱ ደንብ" የመጀመሪያው መጽሐፍ በባዛንታይን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ባሲል ዘመቄዶንያ በ፰፻፸፱ በታወጀው የሮማውያን ሕግ ዝነኛ መመርያ የፕሮሼሪየን የአረብኛ ትርጉም መሆኑን አማሪ በ፲፰፻፶፱ አካባቢ ተገንዝቧል ።[57] ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፰፻፹፫[58] የተገለጸና በሬዶል[59] የተረጋገጠ ሲሆን ናሊኖ አንቀጽ በአንቀጽ ባደረገው ንጽጽር ከ፩፻ በላይ የሆኑ የፍትሐ ነገሥት ጠስ (TS) ጥቅሶች በአረብኛ የሕግ መጽሐፍ በኩል ፕሮሼሪየን ውስጥ አግኝቷል ።[60] ከግሪክ ወደ አረብኛ የተተረጎመው በ፲፪ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ወይም በ፲፫ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በመለካውያን ይመስላል ።[61]

## ለ/ የሱሮ-ሮማውያን (Syrio-Roman) የሕግ መጽሐፍ

"የነገሥታቱ ደንብ ሁለተኛ መጽሐፍ" "የሱሮ ሮማውያን የሕግ መጽሐፍ" ተብሎ ከሚታወቀው ፣ በተጨማሪ "የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ፥ ቴዎድስየስና ሊዎ ሕግ" የሚል ርዕስ ከተሰጠው ፣ ወደ አረብኛ መተርጎሙን ሳቻ[62] በ፲፰፻፹ ተገንዝቧል ። ይህም ከ፬፻፸፮-፬፻፹ ባለው ጊዜ በግሪክ ቋንቋ ተጠናቅሮ ፣ ወደ ሶርያ ቋንቋ በ፮፻፶ እና ወደ አረብኛ በ፩ሺ፩፻ ተተርጉሞአል።[63]

ሴልብ[64] በቅርቡ ያደረገው ጥናት ቀደም ሲል ከተሰጡ ትርጉሞች በመቃረን[65] ፤ በመሠረቱ በሮማ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ምሥራቅ ክፍል በሥራ ላይ የዋለ የሮማ ሕግ መግለጫ እንደሆነና ምናልባትም ለማስተማርያነት እንዲያገለግል እንደተጻፈ አመልክቷል ።[66] ይህም ምንጭ በፍትሐ ነገሥቱ ውስጥ ፹፱ ጊዜ መክ (MAK) ተጠቅሶአል ። ደ ኤሚልያ በጣም ጠቃሚ ስለሆነው ሽያጭን ስለሚመለከተው አንቀጽ ባደረገውም ጥናት የፕሮሼሪየንና የሱሮ-ሮማን አዝማሚያ እንዳለበት አሳይቷል ።[67]

## ሐ/ ኤክሎጋ (Ecolga)

በፍትሐ ነገሥቱ ውስጥ ከተጠቃለሉት መጻሕፍት ምንጩን ለመለየት የሚያስቸግረው ሦስተኛው መጽሐፍ ሲሆን ይህም ከኢብን አል-አሳል የምንጭ አመለካከት ግራ የሚያጋባ መሆን በከፊል የሚመነጭ ነው ። ሬዶልና ናሊኖ ሦስተኛው መጽሐፍ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ የሆኑ ሥጋዊ ሕግጋት (ከነዚህም አብዛኛዎቹ የጋብቻ ጉዳይን የሚመለከቱ የሠለስቱ ምዕት (ኒቂያ) ሕግጋትና ትዕዛዝት) (Sanctorum Patrum 318 (Nicaenorium) Sanctiones et Decreta)[68] የአረብኛ ትርጉም መሆኑን ገምቷል ። በሌላ በኩል ግን ፍትሐ ነገሥት ውስጥ ያሉት ፵፫ መጅ (MAG) ጥቅሶች ፣ ጋብቻ ፣ ውርስ ፣ የወንጀል ሕግ ፣ ጥገኝነትና ሥነ ሥርዓትን ጨምሮ ስለ ሕግ ጉዳዮች በዝርዝር የሚያወሱ ናቸው ። ኮስታንዞ[69] በ፲፱፻፵፯ አንቀጽ በአንቀጽ ያደረገው ትንታኔ ቢያንስ ፳፬ የመጀ (MAG) ጥቅሶች ፣ ኢብን አል-አሳል[70] የሚያውቀው መሆኑን ናሊኖ ባያምንበትም ከሌላ የታወቀ የሮማ የሕግ መጽሐፍ መመሳሰሉን አመልክቷል ። ይህም የታወቀው የሕግ መጽሐፍ በባዛንታይኑ ንጉሠ ነገሥት እሶርያዊ ሊዎ ሳልሳዊ እና በልጅየው (እንደራሴውም) በቆስጠንጢኖስ አምስተኛ ኮፕሮንያሞስ[71] የታወጀው "ኤክሎጋ" (ምርጥ) የሚባለው ነው ። ጥቅሶቹ ቀደም ሲል ከነበረ የኤክሎጋ የአረብኛ ትርጉም በማውጣጣት መላካውያን በ፲፫ኛው ምዕተ ዓመት[72] ባዘጋጁትና የኒቅያ ደንቦች በተጠቃለሉበት ጽሑፍ የተመሠረተ ይመስላል ።

ከፍትሐ ነገሥት ክፍሎች እስካሁን ምንጩ ሳይታወቅ የቀረው አባሪው ብቻ ነው ። ይህም "የእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ቄርሎስ ከጳጳሳት ፣ ከዳኞችና ባላባቶች ጋር ያበጁት የውርስ ምዕራፍ" የሚባለው ነው ። ይህ በ፲፪፻፴፭ የታወጀውና ስለዚህም በቀዳሚው የኢብን ኤል አሳል የአረብኛ የሕግ መጽሐፍ የማይገኘው ምዕራፍ ከቄርሎስ ሳልሳዊ ኢብን ላቅላቅ ደንቦች የውርስ ምዕራፍ ቃል በቃል ወደ ግዕዝ የተተረጎመ ነው ።[73] እነዚህም ደንቦች በኢብን አል-አሳል የተረቀቁ ሊሆኑ ይችላሉ ።[74] ፍትሐ ነገሥቱም ውስጥ በድጋሚ የተጠቀሰው እነዚህ ክፍሎች የአባ ኮስማስ ምናልባትም በ፱፻፴፫ ያረፉት ፓትርያርክ ኩዝማን ሳልሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ ፤ ጽሑፎችና ከላይ ከተጠቀሱት የባዛንታይን ምንጮች ተመሳሳይ የሆኑ በውል ባልታወቁ አንዳንድ የሕግ መጻሕፍት የተመሠረቱ ናቸው ።

የፍትሐ ነገሥቱ አባሪ[75] የአማርኛ ማብራሪያ ከኮስማስ ሌላ አባ ገብርኤል የሚባል ሰው ሲጠቅስ ፣ ይህም የውርስ ዝርዝር ዓይነቶችንና ደረጃዎችን (ለንጉሠ ነገሥት ቆስጠንጢኖስ) የሚሰጠውን እና በተለይም "የነገሥታቱን ደንብ" እንደምንጩ የሚያመለክተውን የኮፕት ፓትርያርክ ገብርኤል ዳግማዊ ኢብን ታሪክን (፩ሺ፩፻፴፩-፩ሺ፩፻፵፭) የውርስ ሕግጋት መጥቀሱ ሊሆን ይችላል ።[76]

## የእስልምና አዝማሚያ

በመጨረሻም የሕግ መጽሐፍ ደራሲ የኖረበትንና የጻፈበትን ፖለቲካዊና ባሕላዊ አካባቢ ፣ ይህም የኮፕት ማኅበረ ሰብ ከሰባተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ሲገዛ የቆየበትን የእስልምና ሥልጣኔ ያንጸባርቃል ። በታወቁ የትምህርት ሃይማኖት ምክንያቶች ኢብን አል-አሳል የእስልምና ምንጮቹን ባይጠቅስም[77] በተለይም ሽያጭን ፣ ጉልትን ፣ ፍችን ፣ የወንጀል ቅጣትንና ሥነ ሥርዓትን[78] የሚመለከቱት የሕግ መጽሐፍ ድንጋጌዎች በቀጥታ ከእስልምና ሕግ የተወሰዱ (በይበልጥ ከመለካውያን ትምህርት ቤት[79]) መሆናቸው ተረጋግጧል ። የእስልምናና የሮማ ሕግጋት ጎን ለጎን ሲታዩ ፣ ለምሳሌም ከጥንታዊው የውርስ ሕግ በፊት እንደነበረው ሕጋዊ ድርሻ (portio legitma) በእስላም የኑዛዜ ሕግ[80] እንዳለው "የሚተው ሩብ (ድርሻ)" እና በሽያጭ ሕግ እንዳለው "በጋራ መኖር" ዓይነት አልፎ አልፎ ይገኛሉ ።[81]

ፍትሐ ነገሥቱ መሠረታዊ ድንጋጌዎችን ከአረብኛ ከመቀበሉም በላይ የሕግ ቲየሪ አቀራረቡም የአረብኛ መሠረት እንዳለው በግልጽ ያንጸባርቃል ። የአርዕስቱ ዝግጅት ከሮማውያን ይልቅ የእስልምናን ሥርዓት እንደሚከተል ፣ ምግብንና ልብስን የሚመለከቱ ክፍሎችም መጨመር ከሮማውያን የፍትሐ ብሔር ሕግ (ius civilie) ይልቅ ፊቅን (fiqh) እንደሚቀርብ ናሊኖ[82] አመልክቷል  ሕግን እንደ ሃይማኖት ክፍል መቁጠር በእስልምና የተለመደ ሲሆን [83] ይህ ለሮማውያን የሕግ ሊቃውንት እንግዳ ነገር ነው ። የፍትሐ ነገሥቱም የአጻጻፍ ዘዴ የእስልምና የሕግ ሊቃውንት አቀራረብ ባሕርያዊ ገጽታዎች ይታዩበታል  ኢብን አል-አሳል ለሕግ መጽሐፍ ያበረከተው አስተዋጽኦ ከታመኑ ምንጮች በማውጣት በማውረድና በማመሳሰል መሆኑን በመግቢያው ገልጾአል ፣ ይህም የኩያ (quiyas) የእስልምና የሕግ ሊቃውንት የአሠራር ስልት በግልጽ የሚከተል ሲሆን ስለውርስ የሚደነግገው አባሪውም "የእስክንድርያው ፓትርያርክ አባ ቄርሎስ ከጳጳሳት ፣ ከዳኞችና ከባላባቶች"[84] ጋር ያበጁትን ሕጎች መጨመሩ ከኢጅማ (ijma) የእስልምና ሕግ ቲዎሪ ባልተለየ መንገድ ሥልጣኑን ከተባበረ ስምምነት ያገኘ መሆኑን ያመለክታል ።[85]

የሮማ ሕጎችን በእስልምና ሥርዓት ማበጀቱ የተሳካው አረብኛ የሮማን የሕግ ቃላት ለመገልበጥና ለማዘጋጀት በማመቸቱ ነው ።[86] ይህን አሠራር ከውርስ ሕግ ቃላት ምሳሌ በመጥቀስ ማሳየት ይቻላል ። የግሪኮ-ሮማን የሕግ ጽሑፎች ፋልኪደን (falkidion) በሮማውያን "ሌክስ ፋልሲደያ" (Lex Falcidia) ከሚለው የተወሰደ በኑዛዜ መሠረት በሚደረግ ውርስ ስለሚኖር የማይቀር ድርሻ የሚያመለክት የግሪክ መጠሪያ ነው ።[87] የአረብ ትርጓሜዎችም በአረብኛው የፕሮሽሮን (Procheiron) ቅጅ መጨረሻ ልዩ ማስታወሻ ላይ ፋልኪዲዮን (falkidion) ወይም ፋልኪድ (ffalkid) በማለት ቃል በቃል ተርጉመውታል ።[88] የኢብን አል አሳል የሕግ መጽሐፍ ይህን ዓይነቱን ማብራሪያ በድጋሚ ያልጠቀሰው ጽንሰ ሐሳቡ በዘመኑ በሚገባ "አረባዊ" ስለሆን የግብፅ የሕግ ባለሞያዎች ይረዱታል በሚል ግምት ሳይሆን አይቀርም ፣ ሆኖም መጽሐፉን ወደ ግዕዝ የተረጐመው ሰው ፋልኪደን (falkidion) የሚለውን ቃል በቀጥታ ያለማብራሪያ መገልበጡ ቃሉን ትርጉም ሳያሳጣው አልቀረም ። በ፲፱፻፷፮ በወጣው የፍትሐ ነገሥት እትም የአማርኛ ማብራሪያ ይህን እንግዳ የሆነ ቃል "ውርስን የሚያስተላልፍ" ማለትም አውራሽ ሲል ገልጾታል ።[89]

በሮማ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ምሥራቅ አውራጃዎች እንደሚታወቀው በሮማውያንና በእስልምና ሕግጋት መሐከል የነበረው በይነ ግብር (interaction) በዚህ የሕግ መጽሐፍ ይዘትና የጽንሱ ሐሳብ አደረጃጀት ተጽዕኖ ኖሮት ይሆናል ።[90] ሀበርላንድ በማጠቃለያው ፍትሐ ነገሥቱ "በእስልምና ሕግ የተመሠረተ ነው ፤ ይህም የእስልምና ሕግ ከሮማና የግሪክ ሕግ[91] (ius gentium) የመነጨ ነው " ሲል የሰጠው አስተያየት መሠረታዊ የሆነውን ነገር ያዛባል ። ያም ሆነ ይህ የዌንገርን ዝነኛ አባባል ማጤን ብልህነት ሳይሆን አይቀርም ።[92] "በአረብኛ ሰነዶች የሮማንና የባዛንታይንን የሕግ ቅርስ ወይም በሮማና በባዛንታይን ቅርስ አረብኛ ያለውን ተጽዕኖ ለማመልከት የሚሞክር ሰው የሮም ፣ የባዛንታይንና የአረቦች ታሪክ ፣ ቋንቋና ሕግ ሊቅ መሆን ይገባዋል ወይም ብዙውን ጊዜ በሚደራረቡ በነዚህ ሳይንሳዊ የትምህርት ክፍሎች ነፃ አስተያየቱን ሊሠንዝር የሚችል መሆን አለበት ። ለቀረነው ግን ከምርምር ተዛምዶ ያለው ብሩህ ሕሊና ብቻ ይተርፈናል ፤ ይህም ጥቂት የሥነ ጽሑፍ ማገናዘቢያዎችን ማቅረብ ብቻ ይሆናል ።"

## ማጠቃለያ

በፍትሐ ነገሥቱ ሁለተኛ (ሥጋዊ) ክፍል ተጽዕኖ ስለነበራቸው ምንጮች የተገኙት የሥነ ጽሑፍ ማስረጃዎች ሲጠቃለሉ የሮማ የፍትሐ ብሔር በተለይም ፕሮሽሮን (Procheiron) ዋነኛው ሆኖ ይገኛል ።

ይህ ማጠቃለያ የሽርማንና የዊግሞርን[93] ግምት በከፊል ቢያቅፍም ፍትሐ ነገሥቱ ከጀስቲንያን መጽሐፍ (Corpus Iuris civilis) በጣም የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው ። የተለያዩ ሦስት የግሪክና የሮማውያን የሕግ መጻሕፍት ወደ አንድ የሕግ መጽሐፍ ማቀናጀት ቅራኔዎች መፍጠሩ ግድ ሲሆን ይህም አንድ ወጥ የነበረውን ሥርዓት አፍርሶታል ።[94] ሮማዊ ይዘቱ በየዘመኑ ከወጡ የነገሥታት ሕጎች ለምሳሌ በሲርያና ሮማ በሕግ መጽሐፍ ከታወቁት "ሕገ መንግሥቶች"[95] የተለያዩ አሻል (layers) የተወሰደ ነው ። በተጨማሪም ፍትሐ ነገሥቱ በክርስትና የመለወጥን የተለያዩ ደረጃዎች የሚያንጸባርቅ በተለይም በኤክሎጋ የሚታይና የፕሮሽሮንን ተጻራሪ አቅጣጫ የሚከተል ነው ።[96] በዚህም ዓይነት በምሥራቅ (የሮማ) የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት የተደረገው ቁንጽል አጻጻፍና ቀላል ትምህርታዊ ዘይቤ መልኩን ለውጦታል ።[97] የመጀመሪያዎቹ ሕጎች ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት እንኳን በተከታታይነት ሁለት ጊዜ የተተረጐሙ ፣ በባዛንታይን ግሪክና በኮፕት አረብኛ "ባህል የታነጹ" ፤ በመንፈሳዊም ረገድ በኮፕት አርቶዶክስ ፤ በግዛትና አስተዳደርም በእስልምና ሥር ስለወደቁ ምንጫቸው ከሆነው የሮም ሥልጣኔ ተለያይተው ቀርተዋል ።

ከላይ ከተመለከቱት የማያመቹ ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ የዚህ ቁንጽል የሮማ ሕግ ፍጹም የተለየ ማኅበራዊ አካባቢ ባለው በኢትዮጵያ የተሳካ አቀባበል ማግኘትና እንደሚስማማ መገልበጥ አስደናቂ ነው ። ከ፲፯ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በሚገባ የተጠናቀረውና በአሁኑ ጊዜ ለሚካሄድ ጥናት መሠረት የሆነው ፍትሐ ነገሥት ሕልውናና የማያቋርጥ ዕድገት (ለውጥ) የሕግ ሥርዓቶች በተለያዩ ባሕላት ለመጓዝና ለመዋሃድ ስላላቸው ችሎታ ምሳሌ ይሆናል ።